# የ "አይቻልም" መንፈስ የተሰበረበት ጊዜ

**አሜን ተፈሪ**

### የሺህ አመቱን ድንቅ ሥራ ተመልከቱ

### ከተጀመረው ይልቅ፤ ሊጀመር ያለው ያጓጓል

### ክፍል 2

*እና አንዳንዴ፣ ያለፈ ሥራችንን ሳስታውሰው ትዝ ሲለኝ፣*

*ከተጀመረው ነገር ይልቅ፣ የሚጀመረው ነው እሚያጓጓኝ፣*

*(ፓሮዲ)*

‹‹እንዳያልፉት የለም! ያ ሁሉ ታለፈ፤ ታጋይ የህዝብ ልጅ፤ በደሙ በላቡ ደማቅ ታሪክ ፃፈ›› የሚለው መዝሙር፤ አሁንም ደምቆ ሲያስተጋባ ይሰማኛል፡፡ አዎ፤ ስንቱ ታለፈ!

በክፍል አንድ ፅሁፌ እንዳልኩት፤ ታሪክ ዘወር ብለው ሲያዩት እንጂ ሲሰሩትና ሲያልፉበት ትርጉሙ ብዙ አይታወቅም፡፡ ግን አሁን፤ አንድ ልዩ የታሪክ ሂደት ውስጥ እያለፍን መሆኑን ሁላችንም የምናውቅ ይመስለኛል፡፡ ታዲያ አሁን እያለፍንበት ያለውን የታሪክ ምዕራፍ በውል ለመረዳት፤ ኢትዮጵያን በታሪክ መነጽር መለስ ብሎ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ ሂደን፤ ለአንድ አፍታ በቀይ ባህር ዳርቻ እንቁም፡፡ ቻይና፣ ፋርስ፣ ህንድ እና ግብፅ ደርሰው የሚመለሱ ወይም ሸቀጥ ጭነው ወደነዚህ ሀገሮች ለመሄድ ከአዱሊስ ወይም ከዘይላ ወደብ የሚወጡ ትላልቅ መርከቦችን እንመለከታለን፡፡

‹‹ፍትህ የማጓደልባት›› ወይም ‹‹የአማልክት ምድር›› እያሉ በሚጠቅሷት በዚያች ጥንታዊት ኢትዮጵያ፤ ግዙፍ የንግድና የጦር መርከቦች ይርመሰመሳሉ፡፡ ግን እንቅልፍ አሸልቦን ስንነቃ ያ ሁሉ ነገር የለም፡፡ ሮማ እና ፋርስ ደርሰው ይመጣሉ፡፡ ወዲያ ዘልቀም ቻይና ወደብ ድረስ ሲቀዝፍና ሲነግድ የነበረው ያ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ፤ በስልጣኔው ብዙዎችን ያስቀና የነበረው ያ ታላቅ ህዝብ፤ ጥበብን የተካነው ያ ኢትዮጵያዊ ምሁር ዛሬ ደብዛው ጠፍቷል፡፡ እናም ኃያል የነበረው ያ መንግስት ድንገት ያረጀ አንበሳ ሆኖ ተጋደመ፡፡ በውስጥና በውጭ የገጠመውን ቀውስ መቋቋም ተስኖት ወደቀ፡፡ አሁን በቀይ ባህር መስመር እንደ ድሮው፣ እንደ ልብ መመላለስ አልቻለም፡፡

ዓለምን ያካለል የነበረው ያ ቱጃር ነጋዴ፤ ኃያል የነበረው ያ አክሱማዊ መንግስት ድንገት ተዳክሞ ሲወድቅ፤ በግዙፍ የንግድ መርከብ መቅዘፍና መጓዙ ቀረ፡፡ እኒያ ግዙፍ መርከቦች በወደቡ ዳርቻ በማዕበል እየተናጡ ተገትረው ቆመዋል፡፡ አዱሊስ እና ዘይላ ተገትረው የአይጥ መራቢያና የዓሳ አጥማጅ ልጆች መጫወቻ ሆነው ቀርተዋል፡፡ በመጨረሻም፤ ቀይ ባህር ውጠ አላየሁም ብሏል፡፡ የነበረው ሁሉ እንዳልነበረ ሆኗል፡፡

ያ ታላቅ የባህር ተጓዥ ነጋዴ እንደ ወትሮው ሸቀጥ ጭኖ መጓዙን ትቶ፤ ከባዶ መጋዘኑ በር ተቀምጦ ሲያዛጋ መዋል ጀምሯል፡፡ አንዳንዴ በትናንሽ ጀልባ ሾልኮው ወደ ኢትዮጵያ ከሚመጡ የድሮ ሸሪኮቹ ወይም ጓደኞቹ ጋር ሲገናኝ፤ ‹‹እነ እከሌ እንዴት ናቸው እባክህ?›› እያለ ወዳጆቹን ይጠይቃል፡፡

ስለዚህ ያ ነጋዴ ሁሉን ነገር ትቶ በቤቱ ውሎ ማደር ጀመረ፡፡ የድሮውን ገድል ብቻ የሚያወራና ሲያንጎላጅ የሚውል ሽማግሌ ሆነ፡፡ በመጨረሻም፤ ባለ ፀጋው የባህር ተጓዥ ነጋዴ ሞተ፡፡ ይህን የመጀመሪያው ትውልድ እንበለው፡፡

ቀጥሎ ሁለተኛው ትውልድ መጣ፡፡ የትናንቱ ታላቅ ገድል ገና አልተረሳም፡፡ ይህ ትውልድ፤ በአባቶቹ ደጅ ወድቆ የሚያየውን ብርቅና ድንቅ ቅርስ ሁሉ ያፈረሰውንና ገና ትዝታው ያልደበዘዘውን ጦርነት እያስታወሰ ይቆዝማል፡፡ አንዳንዴም፤ አባቱ ከሮማ ወይም ከቻይና የተገዛውን  ቄንጠኛ ባርኔጣ አድርጎ፤ ውብ ከዘራውን ይዞ ከተማ ወጣ ይልና በአባቶቹ ዕደ ጥበብና ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመጡ የጥበብ ውጤቶች ይቆጫል፤ ይደመማል፡፡ ከተማ ውሎ ሲጨቃጨቅ ውሎ ይመለሳል፡፡ ሌላ ሥራና ሙያ አልነበረውም፡፡ ይህ ሁለተኛው ትውልድ ነው፡፡

ሦስተኛው ትውልድ ተከተለ፡፡ የአያቶቹን የባህር ጉዞና ድንቅ አኗኗር ሲሰማ ማመን ይሳነዋል፡፡ ነገሩንም እንደ ተረት ይቆጥረዋል፡፡ እናም ከተረት የሚቆጥረውን ታሪክ እያወራ ውሎ፤ በአደባባይ ሲንቀዋለል ውሎ ከመዋል በቀር የአያቶቹን የሥልጣኔ ፈለግ መከተል ወይም ማስቀጠል አልቻለም፡፡ ጨርሶ ደነዘዘ፡፡ ሁኔታው በዚህ ቀጥሎ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረው የዚህች ሀገር ተከታታይ ትውልድ (ከነ ልዩነቱ) በሦስተኛው ትውልድ ዓይን የሚታይ ነው፡፡

እንግዲህ በሦስተኛው ትውልድ ዘመን የውጭ ንግድ ቀረ፡፡ የውጭው ንግድ ሲቀር የውስጡም ንግድ ተቀዛቀዘ፡፡ አገር በቀል የሥልጣኔ ሀብቶችና የዕደ ጥበብ ሥራዎች እየተዳከሙ መጡ፡፡ መንግስቱም በውስጣዊ የፖለቲካ ሽኩቻ ቀልብ አጣ፡፡ ከዓመት ዓመት በእሣት ማጥፋት ሥራ ተጠምዶ ቀረ፡፡ መረጋጋትና ፋታ ያጣው መንግሥት ተሳዳጅና ደካማ ሆነ፡፡ የሥልጣኔና የባህል ማዕከል የነበሩት ከተሞች ሁሉ በተከታታይ ጦርነቶች ፈራረሱ፡፡ የዚያ እሳት የላሰ ምሁር፣ ፈላስፋ፣ ነጋዴ ወዘተ የልጅ ልጆች ደነበዙ፤ ፈዘዙ፡፡

በመጨረሻም በዮዲት (ከ858-898) ሥም የሚጠቀሰው ሁነት ተከሰተ፡፡ ከዮዲት የአርባ ዓመታት የአገዛዝ ዘመን በኋላ (?)፤ ሰለሞናዊው ስርወ መንግስት አልሞትኩም ብሎ ዳግም ተነሳ፡፡ ግን አልቻለም፡፡  ለሰላሣ ዓመታት ሲግደረደር ቆየና ተረታ፡፡ ያው እንደምታውቁት፤ ከተሞች በእሳት ጋይተው ወድመዋል፡፡ ነዋሪዎቹም ተፈናቅለው ተበትነዋል፡፡ ንግዱንም ጨርሰው ረስተውታል፡፡ አክሱም፣ አዱሊስና የሃ ወደ ፍርስራሽ ክምር ተቀይረዋል፡፡

በመጨረሻ፤ እነአክሱም ለላስታ እጃቸውን ሰጡ፡፡ ሥመ መንግስቱን ‹‹ዛግዌ›› ብሎ የሰየመው መራ ተክለ ሐይማኖት በላስታ ነገሰ፡፡ ዛግዌና ወራሾቹ ከግሸን፣ ከደላንታ፣ ከኩልመስክ፣ ከቡግና፣ ከላስታ ተራሮች መውረድ አልፈለጉም፡፡ ቅዳሴ እንጂ ንግዱን አልፈቀዱትም፡፡ አልቻሉበትም፡፡ ከዳሸን ተራራ እንደ ቆሙ

ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚካሄደውን የማያባራ የመስቀል ጦርነት እየተመለከቱ ነው፡፡ ‹‹አምላኬ ሆይ፤ ሰላሙን አውርድልን›› እያሉ በጸሎት ይማልላሉ፤ ይማልዳሉ፡፡

የአረብ፣ የፋርስ፣ የህንድ፣ የቻይና እና የግሪክ ቋንቋን አቀላጥፎ ይናገር የነበረው የዚያ እዩር ነጋዴ የልጅ ልጆች (ሦስተኛው ትውልድ)፤ በመንደራቸው ከሚነገር ቋንቋ ሌላ የማያውቁ፤ መሐይም፣ ኋላ ቀር፣ ድሃ እና አፈር ገፊ ሆነው ቀሩ፡፡ ከዮዲት ጀምሮ እስከ ሰባተኛው የዛግዌ ነጋሲ ንጉሥ ላሊበላ (1141-1181) ድረስ ባሉት ሁለት መቶ ሐምሳ ዓመታት፤ ‹‹ሀበሻ›› አንቀላፉ፡፡ እንደ ስድስት ኪሎ የግቢ አንበሳ የታሪኩ ድምፅ ብቻ ያገሳል፡፡ እንዲህ ቆይቶ በላሊበላ ዘመን እንደገና ነፍስ ዘራ፡፡ ሆኖም ላሊበላ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ነገር የሚናፍቀው አይደለም፡፡

ታሪክ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ላሊበላን ተከትለው አራት ነገስታት የዛግዌ ነገስታት ነገሱ፡፡ የሥርወ መንግስት ሽኩቻ ተከተለ፡፡ ሰለሞናዊውን ነጋሲ ይኩኖአምላክ መጣ፡፡ ኢትዮጵያ ፋታ የለሽ የውጣ ውረድ ጎዳና ይዛለች፡፡ የሐይማኖት ጦርነት እና ውዝግብ ረፍት ነስቷታል፡፡ ግራኝም ተነሳ፡፡ ግራኝ ከፊቱ የቆመውን ሁሉ እያሳደደ፤ ልብነ ድንግልን እንደ ህጻን እያባረረ፤ ቆይቶ ሽንብራ ቁሬ ላይ ወደቀ፡፡ ከመስኬቶ አንጋች የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር አብሮ የመጣው አባ ሜንዴዝ በጫረው እሳት፤ የሀገሬ ሰው የፀጋ ልጅ፣ ቅባት፣ ሁለት ልጆች፣ ተዋህዶ እያለ ተላለቀ፡፡

ለአራት መቶ ዓመታት እልቂትን ተሻግረን ጎንደርን በቆረቆረው ዐፄ ፋሲል ዘመን (1635-1670) ትንሽ ቅርስ የሚሆን ነገር ቀረልን፡፡ አፄ ፋሲል፤ በሐይማኖት ከሚለዩት የአካባቢው ሀገሮች ጋር ወዳጅነትን ለመፍጠር ሞከረ፡፡ ደግሞም ከእስክንድሪያ ጳጳስ እንዲላክለትና የባህር በርም ለማግኘት ተጣጣረ፡፡ ሁሉም ሳይሳካላት አለፈ፡፡ በጎንደር የከተሙት ሰለሞናውያን ነገስታት እርስ በእርስ እየተገዳደሉ፤ በሴራ እየተጠላለፉ፤ መርዝ በጠላ እየተሰጣጡ፤ በሚርት፣ በጥላ-ወጊ በጠንቋይና በመፃፍ ገላጭ ድግምት እየተዋጉ፤ ለተከታታይ ትውልድ ዘለቁ፡፡ በመጨረሻ፤ ጨርሶ ደክመው ‹‹ለንጉስ ምፅዋት ጣሉ›› የሚባልበት ሁኔታ ውስጥ ገቡ፡፡ ዘመነ መሣፍንት ተከተለ፡፡ ሀገሪቱ የጦር ዓውድማ ሆነች፡፡ ረጅሙ የሀገራችን ታሪክ አጭር ትረካ ይኸው ነው፡፡ ከዚያ ምን ተከተለ? ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡ ያው ጦርነት ነው፡፡

ዘመነ መሣፍንት በአፄ ቴዎድሮስ መምጣት ተደመደመ፡፡ ግን ሰላም አልተገኘም፡፡ አፄ ቴዎድሮስ፣ የሥልጣኔ ጮራ እንደናፈቃቸው ቀረ፡፡ የውድቀቱ ምንጭ ገብቷቸው ነበር፡፡ ግን አልተሳካላቸውም፡፡ በአጠገባቸው የተገኙትን አውሮፓውያን ‹‹መድፍ ውለዱ›› ብለው በማሰራቸው፤ ‹‹በግዛቴ ፀሐይ አትጠልቅም›› ከምትለው ኃያል ሐገር እንግሊዝ ጋር ተጋጩ፡፡

ወቅቱ የቅኝ ግዛት ዘመን ነበር፡፡ አውሮፓውያን በዘረኛ አመለካከት ታውረው፣ ደካማ ሆኖ ያገኙትን የዓለም ህዝብ ሁሉ ለማስገበር የሚለፉበት ዘመን ነበር፡፡ እንደ ፈጣሪ መመለክ የሚያስቡት አውሮፓውያን በቴዎድሮስ መደፈራቸው ከነከናቸው፡፡ ነገሩ ለብዙዎች አስገራሚ ሆነ፡፡ ‹‹አንድ ቴዎድሮስ የሚባል የጥቁር ንጉስ፤ እንግሊዞችን አስሮ ይዟቸዋል አለ›› በሚል የሚደነቀው በዛ፡፡ ለአንዳንዱ ሰው ይህ የማይታመን ነገር ነበር፡፡ ሌላው ‹‹እንዴት ያለ ጀግና ነው›› እያለ ያደንቅ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ እናት ድህነትና ኋላ ቀርነት ነው፡፡ ድህነትና ኋላ ቀርነት በሀገሪቱ ላይ ያመጣውን ችግር በአፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻ ሰዓት አብነት ማየት የሚቻል ይመስለኛል፡፡  አፄ ቴዎድሮስ ገና ጋሜ ሳሉ፤ እርሳቸው ‹‹ቱርክ›› ብለው ከሚጠሩት የግብፅ ጦር ጋር ገጥመው ሳለ፤ እርሳቸው ጨርሶ አይተውት የማያውቁት የመድፍ ቅንቡላ የቆሙበትን መሬት አንቀጠቀጠው፡፡ በእርሳቸውና በግብፅ ጦር መካከል ያለው ልዩነት የስልጣኔ ልዩነት እንደሆነ ገባቸው፡፡ ከነገሱ በኋላ ከድንቁርና ጋር ጦርነት መግጠም ፈለጉ፡፡ አለ መላ በያዙት ጦርነት የኢንዱስትሪ አብዮት ጀማሪ ከሆነችው እንግሊዝ ጋር ተቀያየሙ፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላ፤ ጀኔራል ናፒር ጦር እና ጓዙን በዝሆን፣ በግመልና በበቅሎ ጭኖ መቅደላ ደረሰ፡፡ ሀገር ምድሩ የከዳቸው አጼ ቴዎድሮስ፤ መቅደላ አፋፍ ላይ ብቻቸው ቁጭ ብለው፤ የ40 ቀን ዕድላቸውን እያማረሩና እየተብሰከሰኩ ቆይተው፤ ‹‹እነዚህን እስረኞች እንፍጃቸው›› ሲሏቸው ከሞት ደጃፍ እንደ ቆሙ በተስፋ መቁረጥ ሳይሆን በማስተዋል ሰሩ፡፡ ‹‹የሀገሬን ሰው እኔ ፈጀሁት፡፡ እና አሁን ሌላ ፍጅት ጥየበት ልሂድ›› ብለው እስረኞቹን ለቀቋቸው፡፡ ከዚያም ለወጉ ያህል ጥቂት ተኩሰው፤ እንደ ንጉስ ሳይሆን እንደ ተራ ሰው በሆነ አለባበስ እንደሆኑ፤ ከእልፍኛቸው ወጣ ብለው፤ ጥቂት አንጋቾቻቸውን አሰናብተው፤ የእንግሊዝ ጦር የመቅደላ አምባን ሽቅብ መውጣት ሲጀምር፤ በባለቅኔው ፀጋየ ገ/መድህን ብዕር

ብለው ምሬት፣ ሀዘን፣ ፉከራና ኑዛዜን በቀላቀለ አነጋገር የምናብ መነባንብ አውርደው፤ ሽጉጣቸውን ስበው አሟሟታቸውን አሳምረው የክብር ሞት ሞቱ፡፡ ተረቱ፡፡ የእንግሊዝ ጦርም መቅደላን ተቆጣጠራት፡፡

የናፒር ጦር አምባውን ሲቆጣጠር፤ ቀድመው የደረሱ ወታደሮች፤ እያጣጣረ የነበረውን ንጉስ አገኙት፡፡ ግን አላወቁትም፡፡ ይህ በምናብ ከሳሉት ቴዎድሮስ ጋራ የሚመሳሰል አይደለም፡፡ እናም ንጉሱ እዚያ መውደቁን አልጠረጠሩም- አልገመቱም፡፡ ይልቅስ፤ በጀርባው የወደቀው ሰው በእጁ የያዛትን ሽጉጥ ወስደው ዘረፋ ለመጀመር ሲሄዱ፤ በሽጉጡ ላይ ያለውን ፅሑፍ አነበቡ፡፡ ‹‹ከእንግሊዝ ንግስት ለአፄ ቴዎድሮስ የተበረከተ›› የሚል ፅሁፍ አዩ፡፡ በመደናገጥ ተመለሱ፡፡

በዚያ ወድቀው የሚያጣጥሩት አፄ ቴዎድሮስ መሆናቸውን አወቁ፡፡ ተመለሱ፡፡ ነፍሳቸው ወጥቷል፡፡ በግፍ መሬት ለመሬት እየጎተቱ፤ የለበሱትን ጨርቅ እየዘነታተሉ፤ ራቃቸውን እስኪሆኑ አስከሬኑን አጎሳቆሉት፡፡ የለበሱትን ደም የተነከረ ሸሚዝ አውልቀው በመውሰድ ተናጠቁ፡፡

አስከሬኑን ቃሬዛ ላይ አጋድመው ፀሐይ እንዲመታውና ወጭ ወራጁ እንዲያየው አደረጉ፡፡ በሬሳ ለማዋረድ ሞከሩ፡፡ በኋላ በጥበቃ ሥር የነበሩት ባለቤታቸው እቴጌ ጥሩወርቅ፤ ‹‹ፍትሐት እንድናደርግላቸው አትፈቅዱም›› ብለው ለናፒር ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ፈቀደላቸው፡፡ ያን ጊዜ አስክሬኑ ከጸሐይ እንዲነሳና የአውሮፓ እስረኞች ከነበሩበት ጎጆ ገብቶ ሸማ እንዲለብስ ተደረገ፡፡ በአምባው በነበረው ቤተመፃህፍት ያገኙትን በሺህ የሚቆጠር ብራና ዘረፉ፡፡ የንጉሱ ዕቃ፣ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ሳይቀሩ ተዘረፉ፡፡ በወታደሮች እና አስቀድመው ቅርስ ለመሰብሰብ አቅደው ገንዘብ ይዘው በመጡ ሰዎች የተዘረፈው ውድ ቅርስ በናፒር ትዕዛዝ ተሰብስቦ ዋድላ ደላንታ ላይ ጨረታ ተካሄደ፡፡ የተገኘውንም ገንዘብ ለወታደሩ አከፋፈለ፡፡

ናፒርን ጨምሮ፤ታስረው የነበሩ ቄሶችም ሳይቀሩ በዘረፋው ተሳተፉ፡፡ የቻሉትን ዘርፈው፤ የቀረውን በየቦታው በትነው፤ ጓዛቸውን ጭነው ጉዞ ጀመሩ፡፡ በኋላ ወንዝ ሞልቶ ሲያስቸግራቸው ከጫኑት እያነሱ በሜዳ ጣሉት፡፡ እቴይቱንና አንድ ልጃቸውን ማርከው ይዘው ነበር፡፡ እቴጌይቱ ከሀገር ሳይወጡ አረፉ፡፡ ልጃቸው አለማየሁ ግን እንግሊዝና ህንድ ሄዶ በብቸኝነት በባዕድ ሀገር ሞተ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሦስተኛው ትውልድ ሰልፍ ለመውጣት ያደረጉት ጥረት አልተሳካም፡፡ በተከታዮቹ ትውልዶች እውን ሊሆን አልቻለም፡፡

ታሪኩን አጭር ለማደረግ፤ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒልክ፣ አፄ ኃ/ስላሴ በኋላም ደርግ እየተከታተሉ በታሪክ ጎዳና አለፉ፡፡ አፄ ዮሐንስ እና አፄ ምኒሊክም በጦርነትና በዘመቻ ዕድሜያቸውን ጨረሱ፡፡  የአውሮጳውያንን ትዕቢት ያስተነፈሰው፣ ለጥቁር ህዝብ ደግሞ የተስፋ ጮራ የፈነጠቀው የአድዋ ድል፤ ዘመን የማይሽረው ገድል መሆኑና በተከታታይ ትውልዶች ሀገራዊ ነፃነታችንን አስከብረን መኳዛችን  እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ እስከቅርብ ጊዜ እንደ ሀገር ለሺህ ዓመታት የያዝነውን የቁልቁለት ሩጫ የሚገታ ሁኔታ መፍጠር እንደ ተሳነን ዘለቅን፡፡

የኢትዮጵያውያን የተጓዝንበት የሺህ ዓመታት የታሪክ ጎዳና ውርደት የዛበት ነው፡፡ ወደ አዘቅት የሚያወርድ ነው፡፡ የውስጥና የውጭ ጦርነት ነው፡፡ ድህነት ነው፡፡ ድንቁርና ነው፡፡ በዚህ ረጅም የማሽቆልቆል ጉዞ፤ ህዝባችን ሰርቶ መብላትን፣ በትጋት ለፍቶ ሀብት ማካበትን፣ ሳይሆን ተረጅነትን ወደ መቀበል፤ ስደትን እንደ አማራጭ ማየትን እንደ ችግር መፍቻ መመልከት የጀመረበት መጥፎ የታሪክ ዘመን ሆኖ አልፏል፡፡

## ልዩ ታሪካዊ ዕድል

አንድ የታሪክ ክስተትና ሁነት ሲሆን ሳለ፤ ክብደቱ፣ ጥልቀቱ፣ ፋይዳውና ትርጉሙ ተሟልቶ አይታይም፡፡ አንድ የተፈፀመ ታሪካዊ ክስተት ብዙ አንድምታና መላ ምት እንደ ተሸከመ ይቆማል፡፡ ከተሸከመውና ከታየን አንድምታ፤ አንዱ የመሆን ዕድልን ያገኝ ይናል- ወይም ሁለቱ- ሦስቱ፡፡ አለያም የታሰበው ሁሉ ቀርቶ ያልታሰበው ሁሉ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡

ሰው፤ በታሪክ ፊት ይህን ያህል ደካማ ነው፡፡ ‹‹ሰው ሲገምት ታሪክ ይስቃል›› ማለት ይቻላል፤ ‹‹ሰው ሲያቅድ እግዜር ይስቃል›› እንዲሉ፡፡ ግን አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ዛሬ፤ በሀገራችን ታሪክ (ቢያንስ ባለፉት አንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ) ቢፈለግ የማይገኝ ልዩና ምቹ ታሪካዊ ሁኔታ (በውስጥ እና በውጭ) አለ እላለሁ፡፡ ይህን በፍጹም እርግጠኝነት እናገራለሁ፡፡ አሁንም አንድ ነገር በእርግጠኝነት እላለሁ፡፡ በሚቀጥሉት አንድ ሺህ ዓመታትም እንዲህ ያለ ዕድል አይገኝም፡፡ በዚህ ቃል ታሪክ የሚስቅ አይመስለኝም፡፡

የአሁኑ ልዩ ሁኔታ በውስጥ እና በውጭ ምቹ ዕድል መኖሩ ብቻ አይደለም፡፡ ባለው ምቹ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል መዋቅር፣ ሰዋዊ ሀብትና ብዙዎቹን በአንድ ያስተሳሰረ የአንድነት ስሜት ተፈጥሯል፡፡ ይህ አንድነት በይዘቱም በጥልቀቱም ፍፁም የተለየ ነው፡፡ ፍፁም ክቡር፣ ፍፁም ታላቅ፣ ፍፁም ጠሊቅ አንድነት ነው፡፡ የተፈጠረው አንድነት አንድ ነገር ዒላማ አድርጎ በማየት የመጣ አንድነት ነው፡፡ በጊዜያዊ ጠላት ላይ ያተኮረ አንድነት አይደለም፡፡ በተሳሳተ አስተሳሰብ በተፈጠረ ምናባዊ ጠላት የተደራጀ አንድነት አይደለም፡፡

ይልቅስ፤ ለሌሎች ጠላቶች አሳልፎ ሲሰጠን የቆየ ዋነኛ ጠላት ላይ ያተኮረ አንድነት ነው፡፡ የህዳሴ አንድነት ነው፡፡ ‹‹ዋናው ጠላታችን ድህነት ነው›› በሚል መሪ ቃል የተፈጠረ አንድነት ነው፡፡

በይዘቱ ልዩ ነው ያልኩት ለዚህ ነው፡፡ መረዳት የሚገባን፤ አሁን ባለፉት ሺህ ዓመታት ያልተገኘ እና በመጭዎቹ ሺህ ዓመታት ሊገኝ የማይችል ልዩ ታሪካዊ ዕድል መያዛችንን ነው፡፡ እናም የዚህ ትውልድ ታሪካዊ ድርሻ ምን እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል፡፡ አንድ የተፍታታ የህዳሴ ሰነድ መያዝ ያስፈልገናል፡፡ ይህም ሰነድ፤ የአሁኑን ትውልድ ታሪካዊ ኃላፊነትና ሚና የሚያመላክት፤ መጭዎቹ ትውልዶችም በምን ዓይነት አመለካከትና አስተሳሰብ እየተመራን የትውልድ ዱላውን እንዳቀበልናቸው በግልፅ እንዲረዱት የሚያደርግ ሰነድ መሆን ይኖርበታል፡፡

የታላቁ መሪያችንን ህልፈት ተከትሎ የተገለጠ ዕድል አለ፡፡ ይህ ዕድል ልዩ መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ አሁን የምንገኝበትን ሁኔታ ከመዋቅራዊ ሁኔታዎችና ከሰው ኃይል አንጻር፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር ብናነፃፅረው ልዩነቱ ፍፁም ጉልህ ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበረው ሁኔታ፤ ‹‹ሲያስቡት-ሲያስቡት›› የሚያደክም ነበር፡፡

ከ20 ዓመታት በፊት፤ ለ30 ዓመታት ከዘለቀ የእርስ በእርስ ጦርነት የወጣ፣ የተፈራቀቀና የተቋሰለ ህብረተሰብ ነበረን፡፡ እንዲህ አይነት የተፈራቀቀ (polarized) ህብረተሰብ፤ የሰከነ ነገር ማሰብ አይቻልም፡፡ በትክክለኛ አቅጣጫ የሚጓዙ ወገኖች እንኳን ከቱማታው ወከባ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በአጭሩ እንደ ማህበረሰብ ‹‹የዕብደት›› ዘመን ነው፡፡

በዚህ ላይ ድህነቱ አለ፡፡ አዲስ ስርዓት የመመስረት ከባድ ሥራም ተጀምሯል፡፡ አማካሪ ነኝ ባዩ ብዙ ነው፡፡ አደናጋሪው ክስተት በየቀኑ ይፈለፈላል፡፡ ደግሞ ፈጣን፣ ለማመንታት ጊዜ የማይሰጥ፣ የፊት የፊቱን ብቻ እንድናይ የሚያስገድድ ጊዜ ነበር፡፡ ራስን ወደ አንድ የሩቅ ግብ የመውሰድ እና ራስን ከጊዜያዊ አደጋ የመጠበቅ ሁለት ፍላጎቶች በእኩል ኃይል የሚጓተቱበት የጭንቅ ዘመን ነው፡፡ የአዲሱን ስርዓት አዲስ መርሆዎች በህይወት የመማርና የመፈተን ዘመን ነው፡፡

ጉዳዩን ሀሳብን በነፃነት ከመግለፅ መብት ጋር አያይዘን እንመልከተው፡፡ የመናገር ነፃነትን የማክበርና በነጻነቱ በአግባቡ የመጠቀም ልምድ በሌለበት ምድረ በዳ የተጀመረ ሥራ ነው፡፡ ከባህል ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው ነው፡፡

የተወዳዳሪ ፍላጎቶችን አካሄድ በአግባቡ የሚያርቅ መዋቅራዊ ሁኔታ የሌለበት የጨዋታ ሜዳ ነበር፡፡ ‹‹survival value›› ጎልቶ በሚወጣበት ሁኔታ፤ የብዙ ተዋናዮችን አሰራርና አስተሳሰብ የሚወስነው ‹‹survival value›› ይሆናል፡፡ እንዲህ ሲሆን self-expresson value ዋጋ ያጣል፡፡ ራስን በመግለፅ እሴት ላይ የተመሰረተው ዲሞክራሲያዊ እሴት ‹‹ነፍስን በማዳን›› እሴት ይታወራል፡፡ ነገሮች ተደበላልቀውና ተሳክረው ያሰክራሉ፡፡ የሀገራችንን የነፃ ፕሬስ የኋላ ታሪክ ማየት ነገሩን ፍንትው አድርጎ ያወጣዋል፡፡

እንደኛ ባለ የታሪክ ጎዳና ያለፈ ማህበረሰብን ወደ ለውጥ ጎዳና መምራት ከባድ ስራ ነው፡፡ ህብረተሰቡ፤ የመንግስት ስልጣን የያዘ ኃይል ሲተች አያውቅም፡፡ ከዚህ ማህበረሰብ የወጡ መሪዎች እሴት ከዚህ የተለየ

የመሆን ዕድሉ እጅግ ጠባብ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማለፉ ለሁሉም ሰው ከባድ ነው፡፡ ሆኖም፣ የኢትዮጵያን የፐሬስ ነፃነት ይዞታ አከፋፍተው ማቅረብ የሚወዱ ሰዎች እንኳን ‹‹ወርቃማው›› ዘመን በሚሉት ሁኔታ ተስተናግዶ አለፈ፡፡ ሸክሙ ግን ወገብ የሚያጎብጥ ነበር፡፡ ሲያስቡት - ሲያስቡት የሚያደክም ሂደት ነበር፡፡

በዚህ ዓይነት ውስጣዊ ሁኔታ ላይ በውጭ ሀገር ድጎማ ካልሆነ የማይንቀሳቀስ ተስፈኛና ተመጽዋች ሀገርን የመምራት ኃላፊነት ከባድ ነው፡፡ ለዚያውም፣ ‹‹ልጅ ራበው ዳቦ ልገዛ ነው፣ አሞታል መድኃኒት ልገዛ ነው›› ሲሉት፣ አይኑ ደም የሚለብስና ‹‹አርፈህ ተቀመጥ!›› ከሚል አበዳሪ ጋር የመደራደር ኃላፊነት መሸከም ከባድ ነው፡፡

ጢት- ማታ ከሚያንገሸግሽ ትዕዛዝና መመሪያ ጋር ‹‹የአራጣ አበዳሪ›› ቦርሳውን ይዞ ከተፍ ከሚል አለም አቀፍ ቢሮክራት ጋር መሟገት ብቻ ሳይሆን፣ ‹‹የህዝቤን ጥቅም አሳልፌ አልሰጥም›› በሚል መርህ የሚመራ መንግስት ይዞ መቆም እንቅርት ያፈርጣል፡፡

‹‹የመንግስት ኩባንያን በቶሎ ወደ ግል ይዞታ አዛውሩ!›› ሲል፣ ‹‹ኧረ ሠራተኛው ይጎዳል፣ ቤተሰቡ ይበተናል!›› ማለትን እንደ ኃጢያት የሚቆጥር ‹‹የልማት አጋር›› እንዴት ያለ ውጋት እንደሚሆን ማሰብ ቀላል ነው፡፡ ‹‹መሬት አይሸጥም፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በአንድ ጀንበር ወደ ግል ይዞታ አዛውሩ የምትሉትን አልቀበልም›› ለሚል መንግስት የመከራ ጊዜ ነው፡፡

በተግባር እጅ እግሩ የታሰረ መንግስት ይዞ እንዲህ ያለ አቋም ማራመድ ፖለቲካዊ ራስን የማጥፋት እርምጃ ይመስል ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ይህን አቋም በፅናት ይዞ መጓዝና ሀገርን ወደ ፈጣን የልማት ምህዋር ማስገባት ከባድ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ትግል ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ሳይሆን፣ የሀገሩ ሀብት በሀገር ሰዎች እጅ የሚገባበትን ሁኔታ ማመቻቸት ምን ዓይነት ልብ የሚያፈስ ነው፡፡ የሀገሪቱ ሀብት ዋነኛ ባለድርሻ የሀገሩ ሰው እንዲሆን ማድረግ ብቻ አይደለም፣ ሐብቱ በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ የሚገባ ሀብት እንዳይሆን የማድረግም ትግል አለ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የሀገሪቱ ሀብት ሰፊ መሰረት ባለው መዋቅር ላይ የተመሰረተና ዘላቂ የሆነ ሀገራዊ የዕድገት ምንጭ በሀገር ቤት እንዲፈጠር ያደረገ አካሄድ ነው፡፡ የዓለምን አካሄድ በርዕዮተ ዓለም እና በተግባር ከወሰነ አመለካከት ጋር በቀጥታ የሚላተም ‹‹አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ›› አስተሳሰብ ይዞ በአደባባይ መቆም፣ እንደኛ በመጥፎ አህጉራዊ ቀጠና ለሚገኝ እና ድሃ ለሆነ መንግስትና ህዝብ እጅግ ከባድ ነው፡፡

ታላቁ መሪያችን እና ፓርቲያቸው ይህን አቋም ይዘው በድል ጎዳና ተረማመዱ፡፡ የዚህ መንግስት አቋም፣ በየሀገሩ እንዳሻው ማዘዝ ለለመደ ኃይል በጣም የሚያበሳጭ ነው፡፡ ‹‹ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም›› በሚልና ለ‹‹ጥጋበኛ›› ማስተማሪያ የሚሆን ቅጣት ለመቅጣት የሚገፋፋም ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ነው የታለፈው፡፡

ጠ/ሚ መለስ በኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ የኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ ላለፉት 30 ዓመታት በድሆች ሀገራት ላይ ያሳረፈው መጥፎ ጠባሳ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ፣ ፈራ - ተባ በሌለው ቋንቋ

እየተናገሩ ሳይ ይገርመኝ ነበር፡፡ ‹‹አሁን ኒዮሊበራሊዝም እንኳን ለኛ ለእናንተም እንደልበጃችሁ እያያችሁት ነው›› አሉ፡፡ በመቀጠልም፤ ‹‹አፍሪካውያን በ1960ዎቹ ከቅኝ ግዛት ያገኙትን ነፃነት ዋጋ የሚያሳጣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ወድቆባቸው ቆይቷል፡፡ አፍሪካውያን የተሟላም ባይሆን በ1960ዎቹ ነፃነት ለመቀዳጀት ያገኙት ዕድል ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው ዓለማዊ ሁኔታ ነፃነታቸውን ወደ ተሟላ ደረጃ ለመውሰድና እስከዛሬ ሲመኙት ያጡትን ብልፅግና ለመጨበጥ የሚችሉበት አዲስ ዕድል አግኝተዋል፡፡ ይህም ዕድል አሁን ካመለጠ ደግም አይገኝም›› ብለው ነበር፡፡

አሁን ዕድገታችን በእነሱ መልካም ፈቃድ የማይወሰንበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህን የማይገኝ ልዩ ዕድል በመጠቀም፤ አሁን ማምለጥ ወይም በድህነት ማጥ ለዘላለም መቀመጥ ምርጫ ሆኖ ከአፍሪካውያን ፊት እንደቀረበ ተናግረዋል፡፡

እንግዲህ ውስጣዊና ውጫዊ ምቹ ዕድል ስል ይህን እያሰብኩ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ያለውን ምቹ ሁኔታ በውል ተረድተን መጠቀም አለብን፡፡ በፍጥነት ለመጓዝ የሚያስችል ህዝባዊ ማዕበልም ተፈጥሯል፡፡ እኛ ይህን ዕድል የማያመክን ትውልድ መሆን ይኖርብናል፡፡ ታሪካዊ ኃላፊነታችንም ምን እንደሆነ መረዳት አለብን፡፡

ጉዳዩ ከዛሬ ሃያ ዓመት የተነሳ አይደለም፡፡ ይልቅስ ሥሩ የዛሬ አንድ ሺህ ዓመት ድረስ የሚሄድ ነው፡፡ በእነዚህ ሺህ ዓመታት ‹‹ከከፍተኛው የስልጣኔ ማማ ወርደን፤ ከድህነትና ኋላቀርነት አዘቅት ገብተናል›› ብለውን ነበር- ታላቁ መሪያችን፡፡ በዚህ ሺህ ዘመናት በየጊዜው ጦርነት ውስጥ እየገባን፤ ቤታችንን በወጉ ማስተዳደር ተስኖን ስንባዝንና በሽታ ስንማቅቅ ነው የምንመለከተው፡፡ ከውስጥና ከውጭ ኃይሎች በተደረጉ ጦርነት የሚማረከው፤ ሁሉ በአረብ ባርያ ፈንጋይ እየተሸጠ በእስያና በመካከለኛው ምሥራቅ የባርያ ገበያ የተሸጠው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ እንዲህ ቀላል እንዳይመስላችሁ፡፡

ይህ ከሺህ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ የሆነ ነው፡፡ እንደውም፤ በባርያ ንግድና በጦርነት እየተጋዙ የሄዱት ኢትዮጵያውያን ከመብዛታቸው የተነሳ በህንድ ጉጅራት እና በየመን መንግስት ያቋቋሙበት ሁኔታ ነበር፡፡ እየቀነሰ ቢመጣም እስከ አፄ ኃይለስላሴ ዘመን ድረስ የዘለቀ መከራችን ሆኖ ቆይቷል፡፡ እንዲውም ከግራኝ አህመድ ጋር በተካሄደ ጦርነት የንጉሱ ልጅ ሚናስ ሁለት የንጉስ እህት ልጆች በባርነት ወደ የመን ተሸጠው እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ የንጉሱ ልጅ በብዙ ወቄት ወርቅና በአጋጣሚ በግራኝ ልጅ መማረክ ምክንያት ሊመለስ ችሏል፡፡ እንኳን የገበሬው ልጅ የንጉሱም ልጅ ከባርነት ያልተረፈበት የውርደት ዘመን አሳልፈናል፡፡ በጦርነት በመጣብን ድህነት እስከዚህ ወርደናል፡፡ ነፃነታችንን አስጠብቀን ቆይተናል እያልን ብንናገርም፤ የጦርነቱም- የባርነቱም መንስዔ የሆነው ድህነት እጁን ከኛ ላይ ስላላነሳ፤ ዛሬም ከዘመናዊ ‹‹ባርነት›› አልተገላገልንም፡፡ ታሪክ ውሉን አልስት ብሎ ዛሬም በአረብ ሀገሮች ‹‹ለግርድና›› በሺዎች ተሰልፈን እየነጎድን ነው፡፡ በእሳት እያቃጠሉን፤ ከፎቅ እየወረወሩን ዓይናችንን ጨፍነን የምንሄደው በድህነት የተነሳ እንጂ ያባት ዕዳ አለብኝ ብለን አይደለም፡፡ አሁን ዋነኛ ጠላታችንን አውቀነዋል፡፡ ድህነት ነው፡፡ ከድህነት መውጫ ቀዳዳውንም አግኝተነዋል፡፡ ከድህነት መጥፎ እስር ቤት ማምለጥ እንደምንችልም በተጨባጭ አይተነዋል፡፡ የባርነትና የውርደት ምንጭ የሆነውን ድህነት የማንበርከኩ ትግል ተጀምሯል፡፡ ከጀመርነው የጸረ- ድህነት ትግል የሚያናጥበንም ነገር እንዳይኖር ምለናል፡፡ ይህ ትውልድ ታሪክ የሰጠውን ዕድልና ኃላፊነት ማወቅ አለበት፡፡ ይህን ኃላፊነትም እንዴት መወጣት እንዳለበት ማወቅ አለበት፡፡

ታላቁ መሪ በአንድ ወቅት እንደተናገረ፤ ‹‹እኛ ጠበንጃ ተኮሱብን ብለን፤ አንተኩስም፡፡ ጠበንጃ የምናነሳው የፀረ- ድህነት ትግሉን የሚያደናቅፍ ጠላት ሲገጥመን ብቻ ነው፡፡ ጥጋበኛ በመንገዳችን ቆሞ ብናየው፤ ከቻልን በጎን ለማለፍ እንሞክራለን፡፡ እንጂ ለምን ተጋደምክ ብለን አንጣላም፡፡ ጠበንጃ አንተኩስም፡፡›› ዋናው ጠላታችን ድህነትና የድህነት ውላጅ የሆኑት ችግሮች ናቸው፡፡ ታላቁ መሪያችን፤ እስከ ዛሬ በተለያየ መልክ እየተመላለሰ ሲያምታታን የነበረውን ጠላት ለይቶና ነጥሎ አሳይቶናል፡፡ ይኸ ጠላት የሚሸነፍበትን ስልትና መርህ ከዝርዝር መመሪያ ጋር ሰጥቶን ተሰውቷል፡፡ እኛም፤ ‹‹የሀፍረትና የውርደት ማቅ አልብሶን የቆየውን ይህን የጠላት መጣልና ማሸነፍ የምንችለው ዛሬ ነው፡፡ አሁን ነው›› ብለን የአደራ ቃሉን አክብረን፤ ሁላችንም እንደ አንድ ህዝብ ሳይሆን እንደ አንድ ቤተሰብ ምለን ተነስተናል፡፡ ለግርድና ወደ አረብ አገር መሰደድ ይቆማል፡፡ ታሪክ ይለወጣል፡፡ ሆ ብለን ለሥራ ተነስተናል፡፡ ‹‹እንግዲህ ምን ይመልሰናል!›› ድህነትም ይሸነፋል! አባይ ይገደባል! መለስ ይታወሳል!